ትምህርት ሚኒስቴር
MINISTRY OF EDUCATION

Press release

መስከረም ١٥ቀን/ 2016 ዓ.ም

**የትምህርት ሚኒስትሩ ክቡር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጉባኤ ላይ የትምህርትን መሰረተ ልማት ማሻሻል የቀጣዩን ትውልድ የወደፊት እድል ማሻሻል መሆኑን ገለጹ።**

የትምህርት ሚኒስተሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በትምህርት ዘርፉ እየተካሄዱ ያሉ ሪፎርሞችን መሰረት በማድረግ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በአሜሪካ ኒውዮርክ ከተማ መስከረም 08/2016ዓ.ም ባዘጋጀው የትምህርት ዘርፍ የጎንዮሽ ጉባኤ ላይ ቁልፍ መልዕክት በማስተላለፍ ተሳትፈዋል።

መድረኩ አለም አቀፉ ማህበረሰብ ድህነት፣ የአየር ንብረት ለውጥ እና በተለያዩ የአለም ክፍሎች የማያቋርጥ ግጭት እና አለመረጋጋትን ጨምሮ ውስብስብ ፈተናዎች ያሉበት በመሆኑ የ2030 የዘላቂ ልማት ግብ (SDG) አጀንዳ  እና ሌሎች የጋራ ተግዳሮቶችን በዘላቂ ልማት ለመቅረፍ አገሮችን አንድ ለማድረግ ያለመ ነው።

በዚህም ሚኒስትሩ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ትምህርት በዲጅታል ዘመን ውስጥ ለልማት፣ ለፍትሃዊነት፣ ለሠላምና ለደህንነት የሚያግዝ ኢንቨስትመንት በሚል በኒውዮርክ ባዘጋጀው መድረክ ላይ ተገኝተው መልዕክት አስተላልፈዋል።

ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በጉባኤው ላይ ባደረጉት ንግግርም ትምህርት ላይ ኢንቨስት ማድርግ ስለ ቀጣዩ ትውልድና አለም ኢንቨስት ማድርግ ነው ያሉ ሲሆን እንደ ሀገርና መንግስት የተለያዩ ሪፎርሞችን በትምህርት ዘርፉ ላይ እየተወሰዱ እንዳሉ አብራርተዋል።

ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት አንጻር ኢትዮጵያ  ካላት ዓመታዊ በጀት 20 በመቶውን ለትምህርት ሥራ እንደመደበች አንስተው ነገር ግን ይህ በጀት ከመንግስት አቅምና በትምህርት ዘርፉ ካለው ውስብስብ ችግር አንጻር በቂ ባለመሆኑ በዚህ ዓመት እንደ ትምህርት ዘረፍ የትምህርት ቤቶችን መሰረተ ልማት ለማሻሻል ያለመ ሀገራዊ ንቅናቄ በመጀመር መላው ህብረተስብ የብኩሉን ሃላፊነት እንዲወጣ እየተደረገ መሆኑንም አንስተዋል።

በኢትዮጵያ ትምህርት ስርዓት ውስጥ በርካታ ችግሮች ቢኖሩም ከዋና ዋና ችግሮች መካከል በትምህርት ቤቶች ውስጥ ምቹ የመማሪያ አካባቢ አለመኖሩ መሆኑን አንስተው አሁን በኢትዮጵያ ካሉት ትምህርት ቤቶች ውስጥ አንድ በመቶ ብቻ አስፈላጊው መሰረተ ልማት የተሟላላቸው መሆኑን ገልጸው አብዛኞቹ ትምህርት ቤቶች መሰረታዊ የሚባሉት መሰረተ ልማቶች ማለትም ንፁህ የመጠጥ ውሃ፣ ተገቢ የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት፣ የቤተ ሙከራ እና አስተማማኝ የኤሌክትሪክ አቅርቦት የሚባሉትን መሰረታዊ መገልገያዎች የሌላቸው መሆኑን አብራርተዋል።

በመድረኩም ትምህርትን በመዋዕለ ንዋይ መደገፍ እስካልተቻለ ድረስ የዘላቂ ልማት ግቦችን ማሳካት ወይም እየተከሰቱ ያሉ ቀውሶችን መፍታት እንደማይቻልም ተገልጿል።

ትምህርት ሚኒስቴር
MINISTRY OF EDUCATION

Press release

ትምህርት ሚኒስቴር በትምህርት ዘርፉ የሚስተዋለውን የትምህርት ቤቶችን መሰረተ ልማት ለማሻሻል ያለመ ትምህርት ለትውልድ የትምህርት ቤቶች መሰረተ ልማት ማሻሻል ህዝባዊ ንቅናቄ በሀገር አቀፍ ደረጃ በማስጀመር እስከ ትምህርት ቤት ድረስ እንዲወርድ ማድረጉ ይታወቃል።

በዚህም እስካሁን በክልሎችና በትምህርት ቤቶች እየተካሄደ ባለው ህዝባዊ ንቅናቄና በተደረገው ሀገራዊ ጥሪ መሰረት በሀገር ወሰጥና ከሀገር ወጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ ባለሀብቶች፣ የቀድሞ ተማሪዎች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማሳተፍ ከፍተኛ ለውጦች እየተመዘገቡ ይገኛል።

ይህ ሀገራዊ ንቅናቄ ግቡን እንዲመታና ለነገው ትውልድ የተሻለ የትምህርት ስርዓትና ትምህርት ቤት ለመፍጠር ድጋፍ ለማድረግ ስለ ትምህርት ቤቶቹ በቀላሉ መረጃ ለማግኘት www.sip.moe.gov.et ፖርታልን መጠቀም ይችላሉ።

በመጨረሻም የትምህርት ቤቶችን መሰረተ ልማት ለማሻሻል አቅሙ፣ ጉልበቱ፣ እውቀቱና ገንዘቡ ያላቸው ኢትዮጵያውያን፣ ባለሀብቶች፣ የቀድሞ ተማሪዎች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የጀመሩትን ድጋፍ አጠናክረው እንዲቀጥሉም ጥሪ ተላልፏል።

ለተጨማሪ መረጃ፡-

እሴተ የሺጥላ ከፍተኛ የኮሙኒኬሽን አማካሪ
ስልክ- 0911235322
ኢሜል--esete.yeshitla@ethernet.edu.et

አመለወርቅ ህዝቅኤል የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈጻሚ
ስልክ 0911235322
ኢሜል-- ameleworkhizkeal@ethernet.edu.et